# የ፬ኢፒር  አሠራርን በተግባር ስለማዋል

ባህር ዳር ዩንቨርስቲ


ታህሣስ ፳፮ ቀን  ፪ሺ፮ ዓ ም

ባንትይሁን ትእዛዙ

# የውይይቱ መርሃ ግብር

- ፬ኢፒር አሠራር ምንነት
- በተግባር ስለ ማዋል
- በየበኩላችን የምናደርጋቸው ዕድገትና ተሳትፎ
- ከሌሎች ጋር ስለምንፈጥረው መተባበር
- ዉይይት፤ ጥያቄና መልስ

# ፬ኢ ፒ ር (4EPR)



ኢኮኖሚ
ያዳበረ
አካባቢን
የተንከባከበ
ምርት
ማጎልመስ
ትምህርትን
ያገናዘበ
በመሓንዲሳዊ
አሠራር
የተቃኘ

# የ4ኢፒር /4EPR/ አሠራር ማለት

- እውቀትንና ግንዛቤን በማስፋት
- ኢኮኖሚና ምጠኔ ኃብትን በማሳደግ
- የተፈጥሮ ሐብትን በመንከባከብና በማለምለም የተመሠረተና
- በመሐንዲሳዊ አሠራር የተዋቀረ
- ምርት ማጐልመሻ ሥነ ምግባር ነው፡፡

በዚህ ዓይነት ስኬትና አጠራር የተሰዬመበት ደግሞ ሦስቱን የሕብረተሰብ ዋና ችግሮች ከሥረ መሠረቶቻቸው ነቅሎ ለመጣል ነው፡፡

ሦስቱ ዋና ወጥመዶች **የዕውቀት ማነስ፣ ድህነትና የተፈጥሮ አካባቢ መላሸቅ** ናቸው፡፡

# የ4ኢፒአር ቁልፍ መሠረታዊ መርሆች

1. ኢትዮጵያ ውስጥ ከ60 ሚሊዮን በላይ የሚገመት ህዝብ ቀኑን በሙሉ ሰርቶ የሚያገኘው አንድ ዶላር በቀን ነዉ፡፡

- ይህ በአደጉት አገር ህዝቦች በቀን ከሚከፈለው ዝቅተኛ ክፍያ 80 ዶላር ጋር ሲወዳደር እጅግ በጣም አሳዛኝ ነው፡፡
- ስለዚህ ከፍ ያለ የገንዘብና የመሳሪያ ግኝት ተካሂዶ ህዝቡም ግንዛቤው ዳብሮና በልዩ ልዩ የስራ መስኮች ላይ ከተሰማራ በመጀመሪያው ሂደት የህዝቡን ምርት በአስር እጥፍ ወይም 10 ዶላር በቀን ማሳደግ ይቻላል ፡፡
- ይህ ዓይነት የምርት እምርታ ብድሩንም ከነ ወለድ/ትርፍ ክፍያው ጋር በአጭር ጊዜ ከፍሎ የህዝቡን ኑሮ በዚያው ልክ ይሻሻላል ማለት ነው፡፡

# ተልዕኮ

የ4ኢ.ፒ.ር ዋና ተልዕኮ የኢትዮጵያ ህዝቦች በሙሉ ግንዛቤያቸውን አሳድገው ራሳቸዉን ለልዩ ልዩ የስራ መስኮች ብቁ በማድረግና በሚዘረጉት ሙያዎች ሁሉ በመሰማራት ምርታቸውን በማጎልመስ ህይወታቸውን በተሻለና ቀጣይነት ባለው መንገድ እንዲመሩ መርዳት / መሳተፍ፡፡

# ዋነኛ ግብ

፬ኢ.ፒ.አር ካወጣቸው አስሩ የመጀመሪያውና ዋነኛው ግብ

- ማንኛዉም ቤተሰብ የኤሌትሪክ ሃይል፤ የቧንቧ ዉሃና የመፀዳጃ አገልግሎት በተመጣጠነ ዋጋ ቀርቦለት ተጠቃሚ ሆኖ ፤ በዘመናዊ የተመሏ ቤት ዉስጥ መኖር ይችላል፤
- እንደ አደጉት አገሮች የሚያስፈልገውን ሁሉ በቅርቡ ካሉ ገበያዎች በመግዛት ቀልጣፋ ኑሮ መኖር ይችላል፤
- ለኢትዮጵያ የሚያስብ ሁሉ ከተባበረ መላው ሕዝቡ በሃያ ዓመታት ከግቡ ይደርሳል።

# የ4ኢፒር አሠራር አምስት ፕሮግራሞች

- 4ኢፒር ሦስቱን ችግሮች ማስወገድ የሚቻለው ሕብረተሰቡ በተሠማራበት መስክ ሁሉ ምርቱን ማጐልመስ ሲበቃና ጊዜውን በሚገባ ሲጠቀምበት ነው፡፡
- የ4ኢፒር አሠራር ምርትን ማጐልመሻ የሚሆኑ ፭ ፕሮግራሞችን አቅርቧል፡፡

1. ከተሞችን መሥራትና ሕዝቡ ከተማ እንዲኖር ማድረግ
2. ኢንዱስትሪ ማስፋፋት
3. ግብርናን በዘመናዊ መንገድ ማካሄድ
4. የተፈጥሮ አካባቢን መጠበቅና ማለምለም
5. የሕብረተሰቡን ግንዛቤ መማሳደግ፤ እውቀት ማስተማር

# የ4ኢፒአር ቁልፍ መሠረታዊ መርሆች

2. ምርት ሲጎለምስ የምርት ዕጥረትና ችግር የፈጠራቸው እርስ በርስ በመጣላት፣ አለመተማመን፣ እስከመገዳደል የሚያደርሱ ችግሮች ይጠፋሉ፤ ወይም በከፍተኛ ደረጃ ይቀንሳሉ፡፡

   - በምትካቸው ሰላም፣ ህብረት፣ አብሮ መስራት ሲተኩ ለሰላምና ጸጥታ ለመጠበቅ የተመደበውን ወደ ምርት በመሰማራት ዕድገቱ በበለጠ ደረጃ ይጨምራል፡፡

3. ፕሮግራሞች ለኢንቬስተሮች ሶስት ዕድሎች ያሳያሉ፡፡

   - ለሚያመጡት ገንዘብ ትልቅ ትርፍ ከነዋናዉ ከመመለሱ በተጨማሪ የሰው ልጆችን ከችግርና ከድህነት ማውጣት የተፈጥሮ አካባቢዎችና የዓለም የአየር ጠባይ የሚጠበቁበትና የሚያሻሽሉ ተግባሮች ላይ መሳተፍ ናቸዉ፡፡

4. የሰዎች የገቢ ምንጭ ማደግ ራሳቸዉን እንዲያሻሽሉና እንዲቆጥቡም ስለሚረዳ እንደ ድርቅ ላሉ ክፉ ጊዜያትም ሲመጡ ከአለፉት በተሻለ መልክ ተዘጋጅተው በመገኘት ከብዙ ጥፋት ሊድኑ ይችላሉ፡፡

# የህብረተሰቡን ግንዛቤና ዕዉቀት ማሳደግ

- ለሕዝብ ስለ፬ኢ.ፒ.ር ተልዕኮና ስለተሻለ የአኗኗር ዓይነት፤ ምርታቸዉን አሳድገው ሊያገኙትና ሊደርሱበት እንደሚችሉ ግንዛቤያቸውን ማሳደግ ፤

- የሰው ልጆች በተፈጥሮ ያላቸው የማስተዋል፤ የማሰብና የፈጠራ ችሎታ በአግባቡ ከተቀሰቀሰ ከፍተኛ ውጤት እንደሚያገኙ ማስገነዘብ።

- ዋናው ተልዕኮ ህብረተሰቡ በራሱ ጥረት ዘመናዊ ቤት እየኖረ ለራሳሱ እና ለልጆቹ ጤናማ የደስታ ህይወት እንደሚኖረው ቢያውቅ ሁልጊዜ በማሰብ በመመኘት ታትረው ለመስራት ይነሳሳሉ፤ ወደ ሌላ የስራ ዘርፍ ወደ ግንባታ ሥራ ወደ ኢንዱስትሪና በቴክኖሎጂ ተጠቅሞ ምርት ለማብዛት በከፍተኛ ጉጉት ይነሳሉ፡፡

# በታላላቅ ከተሞች ለመኖር የሚገፉፉ ዋና ምክንያቶች

- የሕዝቡን መሠረታዊ አገልግሎቶች፣ ማለትም እንደ ውሃ፣ ኤሌክትሪክ ኃይል፣ የፍሳሽ አገልግሎት፣ ትምህርት ቤትና የጤና አገልግሎት በቀልጣፋና በአነስተኛ ወጪ ለብዙ ሕዝብ ማዳረስ የሚቻለው፡ ከተማ ሲሆን ነው፡፡

- እነዚህ አገልግሎቶች በተናጥል ለሚገኙ መንደሮችና ትናንሽ ከተሞች ለማዳረስ አዳጋችና ከፍተኛ ወጭ የሚያስፈልጋል

- በትልልቅ ከተሞች የተለያዩ የተሰባጠሩ ተደጋጋፊ የሆኑ የሥራ፣ የአገልግሎት፣ የሙያና የንግድ እንቅስቃሴዎች ስላሉ ሰዎች በሚቀናቸው የሥራ መልክ ተሰልፈው የበለጠ በማምረት ከፍተኛ ገቢ ስለሚያገኙ ከገጠሩ አኗኗር እጅግ በጣም ያማረ ኑሮ መኖር ይችላሉ፡፡

- ስለዚህ ትልልቅ ከተማዎችን በመቆርቆር የገጠሩ ሕዝብ ወደ ከተማ ገብቶ የበለጠ በማምረት ኑሮውን ያሻሽል፡፡

# ኢንዱስትሪ ማስፋፋት ዋና ምክናያቶች

- በሀሉም የሀገሪቱ ክፍሎች ኢንዱስትሪዎችን እናቋቁም
- የኢንዱስትሪዎች መቋቋም ለብዙ ሕዝብ የሥራ እድል ይከፍታል፡፡
- የኢንዱስትሪዎችም አብዛኛው ወይም ሁሉም ምርት አገር ውስጥ ተፈላጊ ነው፡፡
- በአሁኑ ጊዜ የመግዛት አቅሙ ስለሌለው ከ85 በመቶ በላይ የሚሆነው የኢትዮጵያ ሕዝብ ኢንዱስትሪ በተሠሩ እቃዎች አይገለገልም፡፡
- ምርቱን ሲያዳብር ገቢውም ሲጨምር የተሻለ ኑሮ ለመኖር የኢንዱስትሪ ምርቶች በሰፊው ስለሚፈልግ አገር ውስጥ መሠራቱ ጥቅሙ እጥፍ ድርብ ነው፡፡

# ኢንዱስትሪ ማስፋፋት ዋና ምክናያቶች...

- ልዩ ልዩ መሣሪያዎች፣ የቤት እቃዎች፣ መድኃኒቶች፣ ኬሚካሎች፡ ፕላስቲኮች፣ የሕንጻ እቃዎች፣ የኤሌክትሮኒክስ እቃዎችና ሌሎችም ለብዙ ሚሊዮን ሕዝብ የሚበቃ ይፈለጋል፡፡

- ይህ ዓይነቱ ፍላጐት ሊዳረስ የሚችለው አገር ውስጥ ሲሠሩ ነው፡፡

- ይህም በአሁኑ ጊዜ 5 በመቶ ብቻ በኢንዱስትሪ ሥራ የተሰማራውን የኢትዮጵያ ሕዝብ ቁጥር ወደ 30 በመቶ ሊያሳድገውና እንደአደጉት አገሮች ሕዝብ የስራ ስምሪት ደረጃ ሊያሳድግ ይችላል፡፡

# ግብርናን ዘመናዊ እናድርግ

- በአብዛኞዎች የለሙ አገሮች ውስጥ በግብርና ሥራ ተሰማርቶ የሚገኘው ሕዝባቸው በቁጥር ከአስር ከመቶ በታች ነው፡፡

- እነዚህ ከአንድ አስረኛ በታች የሆኑ አምራቾች የሚያመርቱት ከአገራቸው አልፎ የዓለም ገበያን ያጥለቀልቃል፡፡

- በኢትዮጵያ ውስጥ ከ80 በመቶ በላይ በግብርና የተሰማራው ሕዝብ የሚያመርተው ግን ለአገሩ ሕዝብ አልበቃ ብሎ በየጊዜው የምግብ ችግርና የምግብ ዋጋ ንረት እያስከተለ ይገኛል፡፡

- ይህም የሆነው የኢትዮጵያ የአየር ጠባይ በዓመት ሦስት ጊዜ ሰብል ማስገኘቱ እየታወቀ ብሎም መሬቱ ለምነቱ እየታወቀ ነው፡፡

- ዋናው ምክንያቱ ግን ባልተሻሻለ መሣሪያና ጊዜ ባለፈበት ዘዴ በመጠቀሙ ነው፡፡

# ግብርናን ዘመናዊ እናድርግ…

- ሕዝቡ ወደ ከተማ ለመግባት እድሉ ቢኖረውና በተለያዩ የሥራ መስኮች ቢሠማራ ጥቂቶች ቀርተው ግብርናውን በዘመናዊ መሣሪያና በተሻሻለ መንገድ ሊያካሄዱና በቂ ሊያመርቱ ይችላሉ ማለት ነው፡፡

- የ4ኢ.ፒ.አር ግብርናን በዘመናዊ መንገድ ማሻሻል ሁለት ዓቢይት መርሆዎችን የያዘ ነው፡፡

1. ለዘመናት አባቶች ለልጅ ልጅ ያስተላለፉት የእንስሳትና እጽዋት እድገት ልምድን በመመርኮዝ

2. ዘመናዊ ብልሃቶችንና መሣሪያዎች መጠቀም ናቸው፡፡

# የተፈጥሮ አካባቢን መጠበቅና መንከባከብ

- በየዓመቱ በብዙ ሚሊዮን የሚቆጠሩ ዛፎች ለማገዶ ያለምትክ እየተቆጠረ ይገኛሉ፡፡
- የእርሻ መሬትን ለመጨመር ጫካዎች እየተመነጠሩ የመሬት ሽፋን እየተገፈፈ ይገኛል፡፡
- ግልጽ የሆነው መሬትም ጠራራ ጸሐይ ነፋስና ዝናብ ሲያርፍበት እየተሸረሸረ ለም አፈር እየተጠረገ በመሄዱ መሬቱ እየደረቀ ነዉ፡፡
- ይህንን ሂደት በአስቸኳይ ማቆም ለህብረተሰቡ ህልውና ቅድሚያ የሚሰጠዉ ጉዳይ ነዉ፡፡

# የተፈጥሮ አካባቢን መጠበቅና መንከባከብ

- እየተቆረጠ ማገዶ የሚሆነዉ ዛፍ የሚፈጥረዉ የካርቦን ጭስ ተጠራቅሞ ጠፈርን እያበላሸ ይገኛል፡፡
- ዛፎችና ጫካዎች የካርቦን ጭስ ማጣሪያ በመሆናቸውና በመጥፋት ላይ ስለሆኑ የአየር ጠባይ መበከል ዓለምን እየጎዳ ይገኛል፡
- ለማገዶ የተለያዩ የሃይል ማመንጮዎችን በመጠቀም ግብርናም በዘመናዊ መንገድ ቢካሄድ የዛፎችን መቆረጥ ያቆመዋል ለዚህም የዓለምን ድጋፍና ትብብር ያስገኛል፡፡

# በተግባር ስለማዋል

1. በቀጥይነት ዕውቀት ማሳደግ ማዳበር
2. ወደግቡ እየተቃረበ ያለው ህዝብ እንዲተጋ ማበረታታት
3. የተሰራውን እየገመገምን ሁሉም እንዲደርሰው ማድረግ
4. ፕሮግራሞችን በመጨረስ ግብን መቀዳጀት
5. ለሌሎች የዓለም ህዝቦችም አርአያ ሆነን መገኘት

1. ግንዛቤንና ተመክሮን ማስፋፋቱን  መቀጠል
2. ህዝቡ የተፈጥሮ ዕውቀቱን ተጠቅሞ ያሳየውን መሻሻል ማስተጋባት
3. ሠርተን በማሳየት ማበረታታት፤ ተመክሮዎችን ማስፋፋት
4. የሌሎችንም ተሳትፎ ማቀናጀት፤ ዕድሎች እንዳያመልጣቸው ማሳየት
5. ፕሮግራሞችን በሰፊው መቀጠል፤ ማሻሻዎችን ዕድገቱን ማዋሃድ

1. ህዝቡ የተፈጥሮ ዕውቀቱን እንዲጠቀም በተለያየና አግባቢያዊ በሆነ መንገድ ማካሄድ
2. ግንዛቤንና ተመክሮን ማስፋፋት፤ የዚህን አሠራር የባለሙያዎች ህብረት መሻት
3. ሠርተን በማሳየት ማበረታታት፤ ኅብረታችን፤ ትጋታችንን ማሳየት
4. የሌሎችንም ተሳትፎ ማቀናጀት፤
5. የፕሮግራሞችን ብህረ ዝግጅት መዘርጋት ሥራም መጀመር

















































Keeping the stack of Teff for a couple of months makes for a better harvest, Teff farmers believe, and thus scenes like the one seen above are common in most parts of rural Ethiopia.











# ማጠቃለያ

በመረዳዳት፤ በመተሳሰብ፤ በመመካከር፤ ግንዛቤ  በማሳደግ ፤ ምርት በማጎልመስ፤ የተትረፈረፈ የጤና የደስታ የሰላም ኑሮ ለመቀዳጀት ሁሉም ሰው እንዲነሳ 4ኢፒር ያሳስባል


- [Feedback](#)

[Contacts](#)

people in rural areas contact

4. Website designers, managers and programmers needed contact
5. It is already being viewed in four continents by growing numbers. Here are some of the comments received.

# Productivity Improvement solves Poverty and Lack of Peace




RATIONALE


90% of a country's economic activity occurs within its boarders. In other words, for every product and service produced in a country, 90% of the consumers are in the country. Demand and supply grow together. Therefore, if productivity of the people rises in every sector, people will earn more and spend more for all the goods and services to lead a better standard of living and the economy grows.

**TOOLS - TECHNOLOGY how can we pay for them to boost productivity?**

We buy and bring in the tools and technology to produce more, build more and improve lives and standard of living. Once we have plenty of food and beautiful facilities, we invite the world for good time. We host them, treat them and feed them in beautiful hotels, restaurants, resorts and entertainment venues. The money they bring for the good time will pay all the debt spend on technology and tools. Win-Win without aid money.

© 2013 by 4EPR.com.

አመሰግናለሁ


ድህነት
አካባቢ መላሸቅ
ዕውቀት/ ግንዛቤ ማነስ
የዓለም ወጥመዶች